# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

ቁጥር 254 መጋቢት 19 2005 ገጽ 1


አንብበው
ያስነብቡ!
አባዝተው
ያሰራጩ!

ወያኔና ሎሌዎቹ ከራሳቸው ጥቅም ውጭ ለማንም እንዳልቆሙ ደጋግመውም ነግረውናል አሳይተውናልም።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ይህ የወያኔ የግፍና የዘረፋ ስርአት እንዲወገድ መታገል ብቻ ሳይሆን ህዝባችን ትግሉን እንዲቀላቀል ጥሪውን ያቀርባል። የወያኔ ግፍኛ ስርአት መቀጠል የሚችለው ህዝባችን እስከፈቀደ ጊዜ ብቻ ነው።

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል አብረን እንታገል የሚል የትግል ጥሪ አደረገ

የኢትዮጵያ ህዝብ ሃያ አንድ አመት ሙሉ ከቀለደበት የወያኔ ኢህአዴግ አገዛዝ እጅግ በጣም የተሻለ አማራጭ ኃይል እንዳለዉና ይህንን ለኢትዮጵያ አንድነት፤ ለህዝቦቿ እኩልነትና ነፃነት በቆራጥነት የቆመዉን አማራጭ ኃይል የኢትዮጵያ ህዝብ በፍጥነት እንዲቀላቀልና የትግሉን የመጨረሻ ምዕራፍ እንዲጀምር የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል አገራዊ ጥሪ አደረገ። የወያኔ ንቀት፤ ጥላቻና ህዝብን ማሸበር ማብቃት አለበት ብለዉ አምርረዉ በተነሱ ወጣቶች፤ምሁራንና ወታደሮች በቅርቡ የተቋቋመዉ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል በላፈዉ ሳምንት እንዳሳወቀዉ በወያኔ ተራ ካድሬዎች መረገጥና እየተገፋ እስር ቤት መወርወር የሰለቸዉ ኢትዮጵያዊና በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ዉስጥ በህዝብ ነጻ ፍላጎት ተመስርቶ ህዝብን በታማኝነት የሚያገለግል ስርአት ለመመስረት ምትፈልጉ ኢትዮጵዉያን ሁሉ ወያኔ እስካለ ድረስ ይህንን ህዝባዊ ስርአት ካለመስዋዕትነት ማምጣት አይቻልምና ለድል ሊያበቃን የሚቸለዉን መስዋዕትነት ለመክፈል እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በተጠንቀቅ እንዲቆም አገራዊ የአደራ ጥሪዉን አስተላልፏል። የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል ይህንን ጥሪ ያደረገዉ የወያኔ ህወሀት ተሸካሚ ፈረስ የሆነዉ ኢህአዴግ ካለፈዉ ቅዳሜ መጋቢት 14 ቀን እስከዛሬ ማክሰኞ መጋቢት 17 ቀን ድረስ ባህርዳር ላይ ጌታዉን ተሸክሞ ያካሄደዉን ትርጉም የለሽ የወሬ ጉባኤ አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ህዝብ ባስተላለፈዉ መልዕክት ነዉ።

ዛሬ የኢትዮጵያን ህዝብ በዘረኝነት ገመድ አስሮ እየረገጠ የሚገዛዉ ወያኔ ለዚህ የበቃዉ በዘረኝነትና በጥላቻ አነሳስቶ ያሰታጠቃቸዉ ገበሬዎች በከፈሉት መስዋዕትነት ነዉ ያለዉ ይሄዉ ህዝባዊ ኃይል ሠላም ወዳዱ የኢትዮጵያ ህዝብ እራሱን ከእነዚህ የቀን ጅቦች ለማላቀቅና አገራችንን የእኩሎች አገር ለማድረግ ማንኛዉንም አይነት መስዋዕትነት ለመክፈል መዘጋጀት አለበት ብሏል። የኢትዮጵያ ህዝብ የጀመረዉ የፍትህ፤ የነጻነትና የዲሞክራሲ ትግል ግቡን እንዲመታ የመጀመሪያዉን እርምጃ የወሰደዉና (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## ከቤሻንጉል ጉምዝ የተፈናቀሉ አማሮች በጨካኙ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ወከባ እየተፈጸመባቸው መሆኑ ተሰማ

ቀደም ብሎ ከቤሻንጉል ጉምዝ የተፈናቀሉ አማራዎች፣ የደረሰባቸው እልቂትና እንግልት ሳያንሳቸው አሁን ደግሞ የመንግስት ባለስልጣናት እያስፈራሩዋቸውና እያዋከቧቸው መሆኑን ተፈናቃዮችን ያነጋገረው ዘጋቢያችን በላከልን ሪፖርት ገለጸ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ተፈናቅለው በምእራብ ጎጃም ዞን በፍኖተሰላም ከተማ ሜዳ ላይ ወድቀው የሚገኙት አማራ ተወላጅ አርሶደአሮች ከክልሉ ዋና ከተማ እና ከዞኑ የተውጣጡ የወያኔ ሆድ አደር ባለስልጣናት ትናንት ሰብስበው ያነጋገሩዋቸው ቢሆንም ፣ ሆድ አደር ባለስልጣናቱ ተስፋ የሚያስቆርጥ መልስና ማስፈራሪያ የሰጧቸው መሆኑ ታውቋል።

ዘጋቢያችን አክሎ እንደገለጸው የወያኔ ሆድ አደር ባለስልጣናት ተፈናቃዮቹን ከተማውን ለቀው ወደ ወረዳቸው እንዲሄዱ ያስጠነቀቁዋቸው ሲሆን፣ የተቀሙትን ሀብትና ንብረት በተመለከተ ጥያቄ ሲያቀርቡ ደግሞ "ቀድሞ ማን ሂዱ አላችሁ አናውቅም" በማለት የመለሱላቸው መሆኑን ገልጿል።
ከቤሻንጉል ጉምዝ ተፈናቅለውና ከሞት ተርፈው ቀያቸው የደረሱትና በገዛ ቀያቸው ያለምንም መጠለያ ሜዳ ላይ ተጥለው የሚገኙት 2 ሺህ አባወራዎች፣ ከንጽህና ጉድለት ጋር በተያያዘ በሽታ ተነስቶ ህጻናትና ሴቶች ሊያልቁ ይችላሉ በማለት ስጋታቸውን በመግለጽ ላይ መሆናቸው ተያይዞ የደረሰን ዘግባ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ደግሞ  አሁንም የቤንሻንጉል ጉሙዝን ክልል ለቀው ባልወጡ አርሶአደሮች ላይ የሚፈጸመው ግድያና እንግልት መጨመሩ የታወቀ ሲሆን የተፈናቃዮችን ሀብት ለመዝረፍ በተደረገ ሙከራ ትናንት አንድ ግለሰብ በጥይት ተመትቶ መሞቱና ሌሎች ሁለት ሰዎች ደግሞ የደረሱበት አለመታወቁን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

ግዜ
ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በደቡብ አፍሪካ ለአባይ ግድብ መዋጮ የጠራው ስብሰባ ተበተነ

በደቡብ አፍሪቃ የሚገኙ ኢትዮጵያዊያን ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ለአባይ ግድብ መዋጮ በሚል የጠራውን ስብሰባ እንዲያቆምና ተሰብሳቢዎችም እንዲበተኑ ያደረጉ ሲሆን ኢትዮጵያውያኑ ይህን እርምጃ ለመውሰድ የተነሳሱት የወያኔን አገዛዝ ቅጥ ያጣ ፖሊሲ በመቃወም መሆኑን ዘጋቢያችን ከስፍራው ባስተላለፈልን ሪፖርት አመለከተ።

ዘጋቢያችን እንደገለጠው ኢትዮጵያኑ የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት በድብቅ ስብሰባ የማዘጋጀታቸውን መረጃ እንዳገኙ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተሰባስበው በመቃማቸው የወያኔ ባለስልጣናት ስብሰባውን በመሰረዝ አዳራሹን ለቀው መውጣታቸውንና በዚሁ አዳራሽ ውስጥ ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊያኑ የራሳቸውን ስብሰባ ማካሄዳቸውን" ገልጧል።

የወያኔ ኢህአዴግ የጠራው ስብሰባ ሮዝባንክ እየተባለ በሚጠራው የደቡብ አፍሪቃ ከተማ  ሲሆን ስብሰባው በልማት ሽፋን የተጠራ እንደነበር ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያመለክታል። ይህን ስብሰባ ለማካሄድ ጥሪዉን ያቀረበው ቴዎድሮስ አድሃኖም ሲሆን ሃያ አምስት የሚሆኑ የወያኔ ኢህአዴግ ደጋፊዎች ስብሰባው ይደረግበት በነበረው ሃያት ሆቴል ቢገኙም ስብሰባው ይደረግበት የነበረውን ሃያት ሆቴል የስርአቱ ተቃዋሚ ኢትዮጵያዊያን  በመሙላትና ስብሰባው እንዳይካሄድ በማድረግ የወያኔ ባለስልጣናትና ደጋፊዎቻቸው እንዲበተኑ አድርገዋል። በዚሁ ስብሰባ የድምጻችን ይሰማ፣ የአነግ፣ የግንቦት ሰባት እና የኢትዮጵያ ኮሚዩኒቲ አባላትና ደጋፊዎች በአንድነት የወያኔ ኢህአዴግ ስብሰባ እንዳይደረግ በማድረግ በልማት ስም ማጭበርበር ይቁም፣ ከልማት በፊት የህዝብ ነጻነት ይቅደም፣ በኢትዮጵያዊያን ላይ እየደረሰ ያለው ግፍና በደል ባስቸኳይ ያቁም፣ በቅድሚያ መገደብ ያለበት ወንዝ ሳይሆን የኢትዮጵያ ህዝብ እንባ ነው የሚል  ጠንካራ ተቃውሞ ማሰማታቸውን  ዘጋቢያችን ባስተላለፈልን ሪፖርት አመልክቷል።

የእለቱን ስብሰባ ሊመራ ወደ ቦታው መጥቶ የነበረው ቴዎድሮስ አድሃኖም ከደጋፊው ህዝብ ጥቃት ይደርስብኛል በሚል ፍራቻ ተደብቆ ከአዳራሹ ያመለጠ ሲሆን የወያኔ ኢህአዴግ ስብሰባ እንዳይደረግ ያስተጓጎሉት ኢትዮጵያዊያን ኢህአዴግ  በከፈለበት የሃያት ሆቴል አዳራሽ ስብሰባ በማድረግ በቀጣይ በአንድነት ስለሚያደርጉት የጋራ ትግል መነጋገራቸው ታውቋል።
በዚሁ እለት በነበረው ተቃውሞ ግጭት አለመነሳቱንና ከኤምባሲው 60 ኪሎ ሚትር ርቀት ላይ ከሚገኘው ከሮዝ ባንክ ከተማም ኢትዮጵያዊያን ወደ ኤምባሲው በመሄድ ተቃውሞአቸውን እንዳሰሙ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

## ወያኔ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ያፈናቀላቸዉ 59 የአማራ ተወላጆች በመኪና አደጋ ህይወታቸዉን አጡ

አማራን ካላጠፉ እንቅልፍ ባይናቸዉ አልዞር ያለዉ የወያኔ ዘረኞች ያፈናቀሏቸዉን ስልሳ የአማራ ተወላጆች ይዞ ይጓዝ የነበረ የጭነት መኪና ተገልብጦ  ሃምሳ ዘጠኙ መሞታቸዉን ተፈናቃይ የአማራ ወገኖቻችንን እየዞረ ያናገረዉ የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በላከልን ዜና ገለጸ። ይህንን ያክል ብዛት ያለዉን ተሳፋሪ ህይወት የቀጠፈ አሰቃቂ አደጋ የደረሰዉ 60 ተፈናቃዮችን አሳፍሮ ይጓዝ የነበረዉ አይሱዙ መኪና ትክሻ በሚባል አካባቢ ጀዴሳ ወንዝ ውስጥ ዉስጥ ገብቶ በመገልበጡ መሆኑን አደጋዉ ከደረሰ በኋላ ወደ ስፍራዉ ተጉዘዉ አካባቢዉን የጎበኙ የአይን ምስክሮች ለዘጋቢያችን የሰጡት መረጃ አመልክቷል። አደጋዉ ከደረሰ በኋላ ቆስለዉ ለተጎዱ ሰዎች የደረሰ ምንም አይነት መንግስታዊ ኃይል አለመኖሩ የሞቱትን ሰዎች ቁጥር ከፍ እንዳደረገዉ አንድ ስማቸዉ እንዳይገለጽ የፈለጉና የአካባቢዉ ግብርና ጽ/ቤት የአዝዕርት ኤክስፐርት ለዘጋቢያችን የገለጹ ሲሆን እንደ ኤክስፐርቱ አባባል የብዙ ህጻናት፤ ሴቶችና አረጋዉያን አስከሬን የሚያነሳዉ ጠፍቶ በወንዙ ዳር ግራና ቀኝ ተበትኖ ለብዙ ሰአታት ቆይቷል።

በሌላም በኩል በትናንትናው እለት የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ኢሳት እንደዘገበው ከቤንሻንጉል ጉሙዝ  ክልል በሀይል ተፈናቅለው ወደ ክልላቸው በመጓዝ ላይ ከነበሩት የአማራ ተወላጆች መካከል ሁለት ህጻናት ታፍነው መሞታቸውን ጉዳዩን በቅርብ የሚከታተሉ የአካባቢው ነዋሪዎች የገለጹለት መሆናቸውን አስታውቋል።

እንደ ኢሳት ዘገባ እያንዳንዳቸው ከ70 እስከ 80 የሚደርሱ የአማራ ተወላጆችን የጫኑ 6 አይሱዙ  (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

## ወያኔን ማመን ቀብሮ ነው

አምባገነን መንግስታት አገዛዛቸውን ለማቆየት ከሚጠቀሙበት ዋነኛ መሳሪያቸው ከሆነው የጦርና የደህንነት ሃይል ውጭ በርካታ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ። ልዩነትን ማራገብና ህዝብን መከፋፈል፣ ማስፈራራት፣ ዜጎች መረጃ እንዳያገኙ አማራጭ ሚዲያዎችን ሁሉ ማፈንና መዝጋት ብሎም የጥቂቶቹን ስብእና በጥቅማጥቅም በመግዛት ሎሌና ጋሻ ጃግሬ በማድረግ፤ እንዲሁም በአገዛዛቸው የተማረረውን ህዝብ የተስፋ ዳቦ ላያድሉት እየጋገሩ ነገ የተሻለ ቀን ይመጣል እያሉ መስበክ ከብዙ ጥቂቶቹ ዘዴዎቻቸው ናቸው።

የሰሞኑን የወያኔ ጉባኤና ያወጣቸውን መግለጫዎች ልብ ብሎ የሚያጤን ኢትዮጵያዊ ሁሉ አንድ ነገር በግልጽ ማየት ይችላል። እሱም የጉባኤዉ ተሳታፊዎችና የወያኔ/ኢህአዴግ መሪዎች የሚጋሩት፤ አብሮ ያቆማቸዉና ከምንም በላይ የሚያያይዛቸው አንድ ነገር ቢኖር ፍርሃታቸው መሆኑ ነው። በአለም ዙሪያ በከፍተኛ ፍጥነት እየናኘ አምባገነኖችን እንደማእበል ከወዲያ ወዲህ እያናወጠ፣ እየጠራረገ በማስወገድ ላይ ያለው የህዝብ የዴሞክራሲና የሰበአዊ መብት መከበር ጥያቄ፣ የእነሱንም በር እያንኳኳ መሆኑ ከፍተኛ ፍርሃት ለቆባቸዋል።

እነዚህ ዘረኛ ቡድኖችና ግፈኞች የሚጋሩት ህዝባዊነት ያለው መርህና የሀገር ራእይ የላቸውም። ለዚህም ነው ጉበኤያቸዉን ሞቶ በተቀበረ ሰዉ መሪ ቃል ጀምረዉ በዚሁ በሞተ ሰዉ ራዕይ የጨረሱት። የዚህ ሰዉ ራዕይ ደግሞ ዘረኝነት፤ስደት፤ እስር፤ ግድያ፤ንቀት፤ዘለፋና ህዝብን ማዋረድ ነዉ። የኢህአዴግ/ ወያኔ መሪዎች የሚያስተዉል አዕምሮ ስለሌላቸዉ አልተረዱትም እንጂ ለኢትዮጵያ ህዝብ በዚህ በዘጠነኛ ጉባኤያቸዉ በግልጽ የነገሩት ነገር ቢኖር ፓርቲያቸዉ ኢህአዴግ የራሱ የሆነ ራዕይ የሌለዉ ጭራሽ በሞተ ሰዉ ራዕይ የሚንቀሳስ ሙት ፓርቲ መሆኑን ነዉ።

የወያኔ ጉጅሌ  ከዘረኝነት ውጭ መኖር እንደማይችል ያውቃል። ወያኔና ጉጅሌዎቹ በሙሉ የሚመኙት በዝርፊያ የደለበው ሀብታቸውና ምቾታቸው እንዲቀጥል፣ ሌላው ህዝብ በገዛ ሀገሩ ሁለተኛ ዜጋ ሆኖ ክብሩን አዋርዶ መኖር መቀጠል አለበት ብለው ያምናሉ። የወያኔ መኳንንት; ኪስ እንዲደልብና ጓዳው እንዲደራጅ፣  በልማትና ትራንስፎርሜሽን ስም ሌላው ህዝብ  መሬትና ንብረቱ መዘረፍ አለበት። ወገን ከአያት ከቅድመአያቱ  ያገኘውን መሬት ለህንድና ለአረብ ቱጃሮች እያስረከበ መሰደድ አለበት። የኢትዮጵያ ህዝብ ልጆቹን በርሃብ ጠኔ እየቀጣ፣ እያስራበ፣ ህዝቡ የወያኔ ገዥዎችን ልጆች ፈረንጅ ሀገር ከፍሎ ማስተማር አለበት። በኢትዮጵያ ህዝብ ስም የሚመጣው ብድርና እርዳታ ሁሉ የወያኔ ቱጃሮች ማድለቢያ፣ መጨፈሪያ መሆኑ ይቀጥላል።

በወያኔኛ እድገትና ትራንስፎርሜሽን ማለት ይሔ ነው። የመለስ ራእይ ማለት ባለፈው 21 አመት ያላየነው ምትሃት አይደለም። ሰፊውን የሀገራችንን ህዝብ የበይ ተመልካችና አጨብጫቢ አድርጎት የኖረው የመለስ ዜናዊ ዘረኛ የ21 አመታት አጅንዳ ነው። የወያኔና የሎሌዎቹ የጉባኤ መደምደሚያ ውሳኔ የቃላት ጋጋታ፣ ተበትኖ ሲፈተሽ ትርጉሙ "ላለፉት ሁለት አስርተ አመታት በገዛ ሀገራችን እንደ ሁለተኛና ተዋራጅ ዜጋ አድርጎን የቆየው አጅንዳ ተጠናክሮ ይቀጥላል፣ ግድያው ና እስራቱ ይጨምራል፣ አርፋችሁ እየተዋረዳችሁ እየረገጥናችሁ የምናደርገውን ጉዞ እንቀጥላለን" ማለት ነው።

ወያኔና ሎሌዎቹ ከራሳቸው ጥቅም ውጭ ለማንም እንዳልቆሙ ደጋግመውም ነግረውናል አሳይተውናልም።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነጻነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ ይህ የወያኔ የግፍና የዘረፋ ስርአት እንዲወገድ መታገል ብቻ ሳይሆን ህዝባችን ትግሉን እንዲቀላቀል ጥሪውን ያቀርባል። የወያኔ ግፍኛ ስርአት መቀጠል የሚችለው ህዝባችን እስከፈቀደ ጊዜ ብቻ ነው።

ዛሬ በርካታ የሀገራችን ወጣቶች በወያኔ ዘረኛ ስርአት ተማረውና ተሰቃይተው፣ የጠባቡ ቡድን አባል ካልሆናችሁ ዳቦ ከቶ አትቆርሱም ተብለው ተገፍተዋል። የነጻነት ሃይሎችን ልሳን ሰምታችኋል፣ የመብት ጥያቄ ጠየቃችሁ፣ ተሰበሰባችሁ፣ በሚል ከውድ ሀገራቸው መሬት የተባረሩት ወጣቶች፤ ይህ ግፍኛ ጨቋኝ ስርአት ያቆም ዘንድ በእኛ ይብቃ ብለው ራሳቸውንና ሀገራቸውን ነጻ ለማውጣት በሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫ ወያኔን ለመፋለም ቆርጠው ተነስተዋል። ታዲያ ህዝባችን በመለስ የተጀመረውና አሁን በጉባያቸው ያረጋገጡልንን አዋርዶና በዘር ከፋፍሎ የመግዛት ራእያቸውን ለማስቆም፣ ሰቆቃን በኢትዮጵያ ምድር ለማብቃት  ከተነሱት ውድ የኢትዮጵያ የቁርጥ ልጆች ጋር  አብሮ መሰለፍ እና ትግሉን መቀላቀል ወቅቱ የሚጠይቀው ኢትዮጵያዊ የሞራል ግዴታ ነው እንላለን፡፡

**ድል ለኢትዮጵያ ህዝብ!!**

---

## ጋዜጠኛ እስክንድርና አቶ አንዱለአም ፍርድ ቤት ሳይቀርቡ መቅረታቸው ታወቀ

በግፈኛውና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በቃሊቲ እስር ቤት የሚገኙት ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋና አቶ አንዱአለም አራጌን ፍርድ ቤት ሳያቀርቡ መቅረታቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ።

የወያኔው አሻንጉሊት ፍርድ ቤት በ አቶ አንዱ አለም አራጌ የክስ መዝገብ በፌደራል ከፍተኛው ፍርድ ቤት በሽብርተኝነት ወንጀል የተፈረደባቸውን የ አንድነት ፓርቲ ም/ል ሊ/መንበር እና የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ አቶ አንዱአለም አራጌ፣ የአንድነት አመራር አባል ናትናኤል መኮንን፣ ጋዜጠኛ እስክንድር ነጋ፣ የቀድሞው የፓርላማ ተማራጭ አቶ አንዱአለም አያሌው፣ የመኢዴፓ ፓርቲ የህዝብ ግንኙነት ሀላፊ አቶ ክንፈሚካኤል ደበበ ፣ አቶ ዮናስ ተረፈ፣ እና ሻምበል የሽዋስ ይሁን አለም የይግባኝ አቤቱታ በአግባቡ አለመመርመሩን መግለጹን የደረሰን ዘገባ ያመለክታል።

በእለቱ ይህን የፍርድ ሂደት ተብየ ለማድመጥ የተከሳሽ ቤተሰቦች፣ የአገር ውስጥና የውጭ አገር ጋዜጠኞች፣ የሰብአዊ መብቶች ተሟጋቾች እና የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች በርካታ ወጣቶች የተገኙ ቢሆንም፣ ዳኛው አቃቢ ህጉንና የተከሳሽ ጠበቆችን ጠርቶ በማነጋገር ጥቂት ጋዜጠኞች ብቻ ችሎቱን መታዘብ እንዲችሉ ማድረጉን ዘጋቢያችን አክሎ ገልጿል።

በእለቱ ችሎት የተሰየመው ዳኛ  ዳኘ መላኩ ብቻ የነበረ መሆኑን የገለጠው ዘጋቢያችን የተከሳሽ ጠበቆችን "እናንተ ምንም የምታምኑት ነገር የለም፣ አቃቢ ህግ ያለምንም የሰው  እና የሰነድ ማስረጃ  ክስ ስላቀረበ ብቻ ነው የተፈረደባቸው፣ እኛ በአግባቡ ተከላክለን እያለ ነው የተፈረደባቸው ስላላችሁ መዝገቡን በአግባቡ ሀ ብለን እየመረመርን ነው፣ በዚህም ላይ የፌደራል ፍርድ ቤት መዝገቡን አዘግይቶ ነው የላከልን ስለዚህ ለእናንተም በአግባቡ ቢመረመር ጥሩ ነው" በማለት መናገሩ ታውቋል።

በዚሁ እለት አንዲት ፖሊስ  ቀርባ  "እኔ የማቅረቢያ የጥሪ ወረቀቱን ለማረሚያ ቤቱ ጸሀፊዎች በአግባቡ ሰጥቻለሁ ለምን እንዲቀርቡ እንዳላደረጉ  አልገባኝም፣ ወረቀቱ አልደረሰንም በማለት ሽምጥጠው ክደዋል፣ በማረሚያ ቤቱ እንዲህ አይነት መካካድ ያለ ነው" በማለት የተለመደ የማደናገሪያ ቃል ተናግራ ፣ ዛሬ የመጣሁት ተለዋጭ ጊዜ ቀጠሮ ለመውሰድ ነው ማለቷን ዘጋቢያችን ገልጿል።

---

## የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል አብረን እንታገል የሚል . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ትግሉ የሚፈልገዉን የደም መስዋዕትነት ለመክፈል የትግሉ ግንባር የመጀመሪያዉ ደጃፍ ላይ የተሰለፈዉ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል ካሁን በኋላ ኢትዮጵያ ዉስጥ የወያኔን ዘረኝነት፤ ዝርፍያ፤ ጥላቻና ንቀት ለማስቆም መፍትሄዉ ከአገር እየተሰደዱ በየባህሩና በየበረሀዉ መሞት ሳይሆን ለስደታችን፤ ለመዋረዳችንና ለመረገጣችን ቀንደኛ ምክንያት የሆነዉን የወያኔ ስርአት እዝያዉ አገር ቤት ዉስጥ ፊት ለፊት በመጋፈጥ ብቻ ነዉ ብሏል።

የወያኔ እህአዴግ ዘመን አብቅቷል፤ከአሁን በኋላ ዘመኑ የኛ የኢትዮጵያዉያን ነዉ ያለዉ የግንቦት ሰባት ዝብባዊ ኃይሎች ቃል አቀባይ ይህንን የኛ የሆነዉን ዘመን እዉን የምናደርገዉና የኢትዮጵያን ህዝብ ከዘረኝነት ነጻ የምናወጣዉ እንደአንድ ሰዉ ቆመን በጋራ ስንታገል ነዉ እንጂ የአገር ማዳኑንና የመስዋዕትነቱን አደራ ለተወሰኑ ወገኖች ብቻ በመተዉ አይደለም ብሏል። በመቀጠልም ወያኔን ፊት ለፊት ተፋልሞ ወንድሞቹንና እህቶቹን ከሁሉም በላይ ደግሞ ከአባቶቹ በአደራ የተረከባትን ኢትዮጵያን ለልጆቹ ለማስተላለፍ የሚናፍቅ ማንኛዉም ኢትዮጵያዊ ከዛሬ በኋላ የት ሄጀ ወያኔን ልታገል የሚል ስጋት እንዳይሰማዉ አሳስቧል። ባለፈዉ ታህሳስ ወር እራሱን (ወደ ገጽ 4 ዞሯል)

---

## ለማያዉቅሽ ታጠኚ

(በማስረሻ መኮንን ከቃሊቲ)

እንደምን ሰነበታችሁ ግንቦቶች - እቺ ደብዳቤዬ እንደምትደርሳችሁ አልጠረጠርም፤ ካልደረሰችም እርግጠኛ ነኝ እናንተዉ ፈልጋችሁ ታገኟታላችሁ። ለመሆኑ እንደምን ከረማችሁ? ዘረኞቹ የወያኔ ካድሬዎች በዚያ ሰሞን ዉጭ አገር ካሉ ሽብርተኞች ጋር ትገናኛለህ ብለዉ ዘብጥያ ወርዉረዉኝ ይሄዉና ሳላናግራችሁ ሳታናግሩኝ ድፍን አንድ አመት አለፈን። መቼም የማይለመድ ነገር የለም መታሰርም ኑሮ ሆኖ ይሄዉና እስር ቤቱን ለመድኩት። ደሞስ የወያኔ እስር ቤት ለምን አይለመድ! ባልታሰር የማላገኛቸዉን ጓደኞቼን፤ ምሁራንንና፤ የእስልምናና የክርስትና እምነት ሊቃዉንትን እዚህ እስር ቤት ዉስጥ ነዉ እንዳሰኘኝ የማገኛቸዉ። ለሁሉም ምን አለፈችሁ ምን አነበብክ፤ ምን ጻፍክ፤ ምን አሰብክ፤ ማንን አሳደርክ እያለ የወያኔ ካድሬ በየቀኑ ከሚጨቀጭቀኝ እዚህ የአገሪቱ ምሁርና አዋቂ የበዛበት እስር ቤት ዉስጥ ብኖር ይሻላል ብዬ አትፍቱኝ ብያቸዋለሁ . . . . . . . የሚሰሙኝ ከሆነ!

ግንቦቶች የዛሬዉ ጉዳዬ የእስር ቤት ኑሮዬን መተረክ አይደለም፤ ጉዳዬ ሌላ ነዉ። ግን ስለ ልጅነት ጓደኛዬ ስለ ታሪኩ ሳልነግራችሁ ባልፍ ቅር ይለኛል። ታሪኩ የወያኔን ፖሊሶች ግልምጫ ከምንም ሳይቆጥር ሁሌ እየመጣ የሚጠይቀኝ የልጅነት ጓደኛዬ ነዉ። ታሪኩ የሚበላ ምግብ ብቻ ሳይሆን የሚነበብ ጸሁፍም ይዞልኝ ይመጣል፤ እኔም የጻፉኩትን ለአንባቢ ያደርስልኛል። የሚገርመዉ ታሪኩ የኮድ ስሙ ሳይሆን እናቱ ያወጡለት ትክክኛ ስሙ ነዉ፤ ስሙን ልደብቅለት ስሞክር . . . ስሜን ይወቁት ምን ያደርጉኛል ብለህ ነዉ . . . . አንተዉጋ ነዉኮ የሚያመጡኝ. . . . . . ደግሞስ በየቀኑ ከምመላለስ አንዱኑ አብሬህ ብታሰር ይሻላል የሚል ቆራጥ ሰዉ ነዉ ታሪኩ።

ጓደኛዬ ታሪኩ በዚህ ሳምንት ይዞልኝ የመጣዉ መጣጥፍ ገና ገልጬ ሳላየዉ ያ እጅ እጅ ያለኝ የኢህአዴግ አርማ ከሩቁ ታየኝና ቀና ብዬ ምነዉ ታሪኩ አልኩት። አንብብ አለኝና ድምጹ ራቀኝ። ምን ሆነ ብዬ ቀና ብዬ ስመለከተዉ ፖሊሶቹ እየገፈታተሩ ከእንግዳ መቀበያዉ ክፍል አስወጡትና ሳይሰናበተኝ ዝም ብሎ ሄደ። እኔም ወደ መኝታ ክፍሌ ገባሁና መጣጥፉን ማንበብ ጀመርኩ። ታሪኩ ሰጥቶኝ የሄደዉ ወረቀት የሚጀምረዉ የኢህአዴግ 9ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ "በመለስ አስተምህሮዎች፤ ጠንካራ ድርጅትና የልማት ሀይሎች ንቅናቄ ለህዳሴያችን" በሚል መሪ ቃል ባህርዳር ዉስጥ ይጀምራል እያለ ነዉ። ወረቀቱ ላይ የሰፈረዉ የዉሸት ብዛት እንኳን እኔን አንባቢዉን ጽሁፉን የተሸከመዉን ግዑዙን ወረቀትም የሚቀፍፈዉ ይመስለኛል። ዮሐንስ ወንጌል ላይ የዉሸቶች ሁሉ አባት የተባለዉ ዲያቢሎስ ትዝ አለኝ። እርግጠኛ ነኝ ወያኔ ያኔ ቢኖር ኖሮ ዉሸት ሌላ አባት ይኖረዉ ነበር። በሦስት ገጾች ተቋጥሮ ከተቀመጠዉ የወያኔ የዉሸት ድሪቶ ዉስጥ አይኔ ያረፈዉ "በመለስ አስተምህሮዎች"፤ "ጠንካራ ድርጅት" ና "የልማት ሀይሎች ንቅናቄ" በሚሉ ሦስት ቱባ ቱባ ዉሸቶች ላይ ነበር። የወያኔዎች ነገር አንዳንዴ በጣም ይገርመኛል። ጥጋባቸዉና ትዕቢታቸዉ ሲፈጠሩ ጀምሮ የተደፈነዉን ጆሯቸዉን ጨምሮ ደፍኖታልና የኢትዮጵያን ህዝብ አይሰሙም እንበል . . . . . . ግን እንዴት የክርስትና እምነታችን መሠረት የሆነዉ ትግራይ አፈር ላይ የበቀሉ ሰዎች ፈጣሪያቸዉን አይሰሙም! እግዚአብሔር እኮ ሃያ አንድ አመት ሙሉ ታግሷቸዉ የገሀዱን አለም የመለስ ዜናዊን አስተምህሮ ብቻ ሳይሆን የአባ ጳዉሎስን የመንፈሳዊ አለም አስተምህሮም ስለተጠየፈ ነዉ ሁለቱንም ሰዎች ተራ በተራ የወሰዳቸዉ። ታድያ መምህሩንና ደቀመዝሙሩን ለሀያሉ እግዚአብሔር ቁጣ ያጋለጠዉን ክፉ አስተምህሮ እንደገና እዚህ ምስኪን ህዝብ ላይ ለመጫን የሚሞከረዉ ለምንድነዉ? ለመሆኑ የመለስ አስተምህሮ ምንድነዉ . . . . . . . ስድብ፤ንቀት፤ ጥላቻ፤ ዘረኝነት፤ኢትዮጵያንና ታሪኳን መጥላት፤ አማራን በየሄደበት ማሳደድ፤ የኑሮ ዉድነት፤ ስደት፤ እስር፤ ግድያ፤ የመሬት ቅርምት፤ ብሔራዊ ዉርደት፤ . . . . . . እስኪ ወያኔዎች እናንተ አራሳችሁ ንገሩኝ ምንድነዉ የመለስ ቅርስ ዬቱ ነዉ የመለስ አስተምህሮ?

ግንቦቶች እዚህ ወረቀት ላይ ካነበብኳቸዉ ነገሮች ሁሉ የሰቀጠጠኝና አይኔን ማመን ያቃተኝ . . . . . . . 9ኛዉ የኢህአዴግ ጉባኤ የአገራችን የልማትና የዲሞክራሲ ጉዞ መሐንዲስ የነበሩት ጓድ መለስ ዜናዊ የሚታሰቡበት ጉባኤ ነዉ" የሚለዉን ሳነብብ ነዉ። ሃያ አንድ አመት ሙሉ የመጻፍና የመናገር መብቶችን አፍኖ፤ የሚቃወመዉን እየገደለና በአንድ አናሳ ብሄረሰብ የበላይነት ዙሪያ 90 ሚሊዮን ህዝብን ረግጦ የገዛዉ መለስ ዜናዊን የዲሞክራሲ መሐንዲስ ማለት ወይ ዲሞክራሲን ወይም ምህንድስናን አለዚያም ሁለቱንም አለማወቅ ይመስለኛል። ደግሞም እዉነቱን ለመናገር መለስን የዲሞክራሲ መሐንዲስ ከማለት መንግስቱ ሀ/ማሪያምን የኢትዮጵያ ፌዴራሊዝም አባት ማለት የሚቀል ይመስለኛል . . . . . . . . ትዝ የሚለን ከሆነኮ ኢትዮጵያ ዉስጥ የመጀመሪያዎቹ የክልል መንግስታት መንግስቱ የፈጠራቸዉ የትግራይ ራስ ገዝ፤ የኤርትራ ራስ ገዝ፤ የአሰብ ራስ ገዝና ኦጋዴን ራስ ገዞች ነበሩ።

ለመሆኑ. .... የመለስን ራዕይ ከግቡ ማድረስ ኢትዮጵያ ህዝብ ምርጫ ቢሆን ኖሮ ለምን አገሩን ለቅቆ እየተሰደደ በየዉቅያኖሱና በየበረሃዉ የእሳት እራት ሆኖ ይቀራል? እሲኪ ንገሩኝ እናንተ ወያኔዎች ምርጫችን የመለስን ፈለግ መከተል ቢሆን ኖሮ ቁጥሩ በብዙ ሚሊዮኖች የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሙስሊም ማህበረሰብ ለምን "ድምጻችን ይሰማ" እያለ በየአደባባዩ በእናንተ ዱላ ይደበደባል? ደግሞስ በየቀኑ ስለማሪያም ስሙኝ እያለ የማትሰሙት የኢትዮጵያ ህዝብ እሱ እናንተን ለምን ይሰማል? እናንተ ወያኔ በአምሳያዉ የፈጠራችሁ የኢህአዴግ ቡችሎች እናንተም ስሙ . . . . . . . . እስኪ ምን ይሁን ብሎ ነዉ የኢትዮጵያ ህዝብ የናቀዉን፤ የሰደበዉን፤ ያዋረደዉን፤ የገደለዉንና በዘረኝነት አለንጋ የለበለበዉን ሰዉ ራዕይ ከግቡ ለማድረስ ቃል የሚገባዉ? ወያኔም ሆነ ኢህአዴግ ወይም አግአዚ ጆሮ ካላችሁ ስሙ . . . . . የኢትዮጵያ ህዝብ ቃል የገባዉ እናንተ በፈቃደኝነት ከተነቀላችሁለት ፈቃዳችሁን ለማክበር አለዚያም እሱ እራሱ ነቅሎ ሊያጠፋችሁ ነዉ።

ኢህአዴግ ለ9ኛዉ ጉባኤ ሲዘጋጅ መሪ ቃል ብሎ ካስቀመጣቸዉ ሦስት ትልልቅ የዉሸት ድሪቶዎች ዉስጥ ሁለተኛዉ "ኢህአዴግ ጠንካራ የፖለቲካ ድርጅት ነዉ የሚለዉ አባባል ነዉ። ነገሩ "ከቀዳዳ ይሻላል ጨምዳዳ".. . . . እንደሚባለዉ ተረት ሆኖ ነዉ እንጂ ገና ከጧቱ ሲፈጠር ጀምሮ ኢህአዴግ መች ጠንካራ ድርጅት ሆኖ ያዉቃል? የኢህአዴግ አባል ድርጅቶች የሚወክሉትን ህዝብ ብዛትና ያላቸዉን የፖለቲካ ጡንቻ ተገንዝበዉ እንቅስቃሴያቸዉን ከፖለተካ ጡንቻቸዉ ጋር ማገናዘብ ቢችሉ ኖሮ እዉነትም የኢህአዴግ ጠንካራ ድርጅት ተብሎ ሊጠራ ይችል ነበር፤የኛም ትግል ወያኔ የፈጠረዉን ስርአት ለመደምሰስ ሳይሆን እንማንኛዉም በሰለጠኑ አገሮች ዉስጥ እንደሚታየዉ የፖለቲካ ህደት ትግላችን በምርጫ ህዝባዊ ሀላፊነትን ለመቀበል ብቻ ይሆን ነበር።ኢህአዴግ በወያኔ አንጎል የሚያስብ፤ በወያኔ አፍ የሚናገርና የወያኔን መንገድ የሚከተል ተሳቢ ድርጅት በመሆኑ ነዉ ዛሬ አገራችን እጅግ በጣም አደጋኛ ቦታ ላይ የምትገኘዉ።

ደግሞስ ዘረኞቹ የህወሀት መሪዎች የዘረፉትን መካፈል አቅቷቸዉ ሲጣሉ፤የኦህዴድ አባላት በአራት ቡድን ተከፋፍለዉ አንዱ የወያኔ ባሪያ ሆነን እንቀጥል ሲል ሌላዉ ደግሞ ነጻነቱን ለማወጅ እየተዘጋጀ ባለበት በአሁኑ ወቅት ምኑ ታይቶ ነዉ የህአዴግ ጠንካራ ድርጅት ነዉ የሚባለዉ? የሚንገዳገዱና በዉስጣቸዉ በተነሳ ቅራኔ የተነሳ ለመፍረስ አንድ ሐሙስ የቀራቸዉን ድርጅቶች ያቀፈዉ ኢህአዴግ እንዴት ሆኖ ነዉ ጠንካራ ድርጅት ሊሆን የሚችለዉ?ባለፉት አምስትና ስድስት ወራት በግልጽ እንደተመለከትነዉ ህወሀትና ኦህዴድ እርስ በርሳቸዉና አንዱ ከሌላዉ ጋር በፈጠሩት ከፍተኛ ቅራኔ የተነሳ ሁለቱ ድርጅቶች የረባ ስብሰባ እንኳን ማካሄድ አልቻሉም፤ እንግዲህ ይህ ኢህአዴግ ነዉ ጠንካራ ድርጅት ነዉ ተብሎ የሚነገረዉ።

ይገርማችኋል በዘመነ ወያኔ ኢትዮጵያ ዉስጥ ሁሉም ነገር የተገላቢጦሽ ሆኗል። ዘላን ለክረምት እንደሰራዉ ቤት ለመፍረስ አንድ ሳምንት የቀረዉ ኢህአዴግ ጠንካራ ድርጅት ተብሎ ይወደሳል፤ የኢትዮጵያ ምሁር መዋያዉ ዩኒቨርሲቲ መሆኑ ቀርቶ ቃሊቲ ሆኗል፤ ጋዜጠኛም መደበኛ ስራዉ መጻፍ ሳይሆን መታሰር ሆኗል።ድምጻችን ይሰማ ብሎ የጮኸ ሽብርተኛ ተብሎ ይታሰራል፤ በምሽት በር እየሰበረ ህዝብን የሚያሸብር ጀግና ተብሎ ይሞገሳል። እንግዲህ ግንቦቶች የወያኔ ጉድ ስንቱ ተዘርዝሮ ያልቃል? እንዲያዉ በደፈናዉ እነዚህ ዘረኞች አገራችንን ጉድ በጉድ አደረጓት ማለቱ የሚበቃ ይመስለኛል።

የጋምቤላን ገበሬ መሬት ለትግራይ ባለሀብት ሰጥተዉ ጋምቤላዉ መሬቴን ሲል "ግንቦት ሰባት" ነህ ብለዉ ይጨፈጭፉታል። ፋሺስት ግራዚያኒ መታሰቢያ ሐዉልት አያስፈልገዉም ብለዉ የተቃወሙ ኢትዮጵያዉያንን አስረዉ መረጃ ካልሰጣችሁንና የብሔር ማንነታችሁን ካልተናገራችሁ አትፈቱም እያሉ ይደበድቧቸዋ። የሚገርመዉ ነጮቹ ፋሺስቶች እንኳን ከ30 ሺ በላይ ኢትዮጵያዉያንን በአንድ ጀምበር ሲጨፈጭፉ ያልጠየቁትን የብሔረ ማንነት ዛሬ ጥቁሮቹ ፋሺስቶች አባቶቻቸዉን የጨፈጨፈ ሰዉ እንዴት መታሰቢይ ይሰራለታል ብለዉ የተቃወሙ ኢትዮጵያዉያንን አስረዉ የዬትኛዉ ብሔር አባል ነህ ብለዉ መጠየቃቸዉ በእርግጥም ማርሻል ግራዚያኒ ሀዉልት ሳይሆን የቆመለት እሱ እራሱ መልኩን ለዉጦ የመጣ ነዉ የሚመስለዉ።

እንግዲህ የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ ልብ ብለህ ነገሮችን አስተዉል . . . . . ኢነዚህ ዳግማዊ ግራዚያኒዎች ናቸዉ በየክልሉ በአምሳያቸዉ የፈጠሯቸዉን አሻንጉሊቶች አቅፈዉና እራሳቸዉን ኢህአዴግ ብለዉ ሰይመዉ ከዛሬ ቅዳሜ መጋቢት 14 ቀን ጀምሮ እስከ ማክሰኞ ድረስ ጉባኤ፤ እድገት፤ ህዳሴ፤የመለስ ራዕይና ትራንስፎርሜሺን እያሉ እያደነቆሩህ የሚከርሙት። እነዚህ ከመልካም አስተዳደር ጋር ሆድና ጀርባ የሆኑ ጉዶች ናቸዉ ሰልመልካም አስተዳደር ለሰብኩህ የሚሞክሩት። ለኢትዮጵያ ህዝብ ስለ ኢህአዴግ ብዙ የሚነገረዉ ያለ አይመስለኝም . . . . . ሃያ አንድ አመት ሙሉ እንደቋጥኝ ተጭነዉበት ጀርባዉን አጉብጦታልና ያዉቀዋል። ኢህአዴግ የራሱ የሆነ ማንነት ያለዉ እዉን የሆነ ድርጅት ሳይሆን ህወሀት የራሱን እዉነተኛ ማንነት ለመሸፈን እንደብረት ቀጥቅጦ የሰራዉ የማታለያ ሽፋን ነዉ። ለዚህም ነዉ በድምሩ 439 የፓርላማ ወንበር ያላቸዉ ሦስቱ የኢህአዴግ ድርጅቶች 38 ወንበር ላለዉ ለህወሀት እየሰገዱ የሚኖሩት። የኢትዮጵያ ህዝብ ሆይ አህያ ሜዳ ለሜዳ ሳሯን እየጋጠች ብትበላ ወይም እንደሰዉ ልጅ ምግብ ተሰርቶላት በሳህን ብትበላ አህያ መባሏ አይቀርም . . . . . . ኢህአዴግም እንደዚሁ ነዉ። ዘጠኝ ግዜ ቀርቶ ዘጠና ዘጠኝ ግዜ ጉባኤ እያለ ቢሰበሰብና የራሱን ብጤ ደካማና አድር ባይ ምሁራንን በየጉባኤዉ ቢያሳትፍ አህያ ለመሸከም እንደተፈጠረች ሁሉ ኢህአዴግም እንደጋሪ ለመጎተት የተፈጠረ ድርጅት ነዉና ኢህአዴግነቱን አይለቅም።ከዛሬ ጀምሮ እስከማክሰኞ ድረስ በቴሌቪዥን የምንመለከተዉ ድራማ አላማዉ አንድና አንድ ብቻ ነዉ . . . . . . እሱም አስቀያሚዉን ኢህአዴግ ሊፕስቲክና የፊት ማሳመሪያ ቅባት እየቀቡ ለኢትዮጵያ ህዝብ ማሳየት ነዉ . . . .መቼም የወያኔ ነገር ጆሮ ለባለቤቱ ባዳ እንደሚሉት ሆኖ ነዉ እንጂ የኢትዮጵያ ህዝብማ ኢህአዴግ ገና ጉባኤዉን ሳይጀምር ነዉ .. . . . . ለማያዉቅሽ ታጠኚ ብሎ የተረተበት።

## ኢትዮጵያ የገጠማት ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሬ እጥረት ወያኔና ነጋዴዉን ማጨቃጨቁ ተነገረ

የተለያዩ የመብት ጥያቄዎችን ለመጠየቅ በደቡብ ክልል በቁጫ ወረዳ ለአቤቱታ የወጡ ከ1000 ያላነሱ ሰዎች በፖሊስ ታግተው መዋላቸውን የአካባቢው ሰዎችን ዋቢ በማድረግ ኢሳት ዘግቧል።

እንደ ኢሳት ዘገባ ከፍትህ፣ ከመልካም አስተዳዳር እና ከመብት እጦት ጋር በተያያዘ በርካታ ጥያቄዎችን ላለፉት 8 አመታት ሲያቀርቡ የቆዩት የቁጫ ወረዳ ነዋሪዎች፣ 7 ወኪሎቻቸው መታሰራቸውን በመቃወም ትናንት አቤቱታ ለማቅረብ ሲሰባሰቡ በፌደራል ፖሊሶች መታገታቸው ከነኝህም ታሳሪ ዜጎች ኢሳት።

ካለፈዉ አመት አጋማሽ ጀምሮ ኢትዮጵያ ዉስጥ በከፍተኛ ፍጥነት እያሽቆለቆለ የመጣዉ የዉጭ ምንዛሬ ክምችት በፈጠረዉ ችግር የተነሳ የንግዱ ህብረተሰብና የወያኔ አገዛዝ ታይቶ የማይታወቅ ጭቅጭቅ ዉስጥ መግባታቸዉን አንድ በቅርቡ ንብረታቸዉን ሽጠዉ ወደ አዉሮፓ የመጡ ኢትዮጵአዊ ነጋዴ ተናገሩ። እኚህ ላለፉት 17 አመታት በዉጭ ንግድ ስራ ላይ ተሰማርተዉ የነበሩ አቶ አህዱ ወሰንየለህ የተባሉ ነጋዴ እንደተናገሩት በአገሪቱ ውስጥ የተፈጠረውን ከፍተኛ የዶላር እጥረት ተከትሎ ነጋዴዎች ላለፉት 8 ወራት እቃዎችን ወደ አገር ዉስጥ ማስገባት አልቻሉም፤ አንደ አቶ አህዱ አባባል በአሁኑ ወቅት ከዉጭ አገር የሚገቡ ዕቃዎችን የሚያስገባዉ የወያኔ አገዛዝ ብቻ ሲሆን አገዛዙ የሚያስገባዉ ደግሞ የግንባታ እቃዎችን ብቻ በመሆኑ የዉጭ ምንዛሬዉ እጥረት የገበያ መዛባት፤ የዕቃዎች እጥረትና የዋጋ ግሽበት እንዲከስት አድርጓል ብለዋል።

ግራ የተጋባዉ የወያኔ አገዛዝ ሰሞኑን ለነጋዴዎች ባስተላለፈው መመሪያ መሰረት በዉጭ ንግድ ዘርፍ ዉስጥ የተሰማራ ማንኛዉም ነጋዴ የውጭ ምንዛሬ ማግኘት እንደሚችል ግልጽ ያደረገ ቢሆንም በአዲሱ መመሪያ መሰረት የውጭ ምንዛሬ የሚጠይቁ ነጋዴዎች በቅድሚያ የጠየቁትን ያክል ገንዘብ በብር ለባንኮች የማቅረብ ግዴታ አለባቸው። ለምሳሌ 100 ሺ ዶላር የሚጠይቅ ነጋዴ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን አምስት መቶ ሺ ብር በቅድሚያ ለባንኮች የማቅረብ ግዴታ አለበት። ይህንን አዲስ አሰራር የንግዱ ህብረተሰብ በፍጹም እንዳልተቀበለዉ የሚታወቅ ሲሆን በነጋዴውና በወያኔ አገዛዝ መካከል ዉዝግብ የፈጠረዉም ይሄዉ አዲሱ መመሪያ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። ኢትዮጵያ ዉስጥ የመለስ ዜናዊን ሞት ተከትሎ ብዛት ያላቸዉ ሰዎች ገንዘብ ማሸሽ በመጀመራቸዉ ከፍተኛ የዉጭ ምንዛሬ እጥረት መከሰቱ የሚታወቅ ሲሆን ባለፈዉ መስከረም ወር ኃ/ማሪያም ደሳለኝ የጠ/ሚኒስትርነቱን ቦታ እንደተረከበ ኢትዮጵያ ዉስጥ ምንም አይነት የዉጭ ምንዛሪ እጥረት አለመኖሩን መናገሩ የሚታወስ ነዉ።

ኢትዮጵያ ዉስጥ የተፈጠረዉን የዉጭ ምንዛሬ እጥረት አስመልክቶ አስተያየታቸዉን እንዲሰጡን የጠየቅነቸዉ አንድ የአኮኖሚክስ ምሁር የወያኔ አገዛዝ የገንዘብ እጥረት ቢያጋጥመው አይገርምም፣ ከመለስ ሞት በኋላ የወጡ ወጪዎችን እንኳን ብናይ፣ ይህች ደሀ አገር ያለአቅሟ በመቶ ሚሊዮኖች የሚቆጠር ገንዘብ አውጥታለች ካሉ በኋላ፤ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ቀብር ማስፈጸሚያ ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ፤ የብሄር ብሄረሰቦች በአል ለማክበር ከ250 ሚሊዮን ብር በላይ የመከላከያ ቀንን ለማክበር ከመቶ ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ ተደርጓል። አሁን በቅርቡ ደግሞ የወያኔ ኢህአዴግን ጉባኤ ለማካሄድና የአባይን ግድብ ሁለተኛ አመት ለማክበር ከፍተኛ ገንዘብ ከመንግስት ካዝና ወጪ ሆኗል ። እንግዲህ እንደዚህ አይነት ከፍተኛ መጠን ያለዉ ገንዘብ ከልማት ጋር ባልተያያዘ መንገድ እየወጣ አገሪቱ የገንዘብ እጥረት ገጠማት ቢባል የሚገርም ሲሆን አይገባም ብለዋል።

## በአረመኔው የወያኔ አገዛዝ በግፍ እስር ቤት የታጎሩት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸው ታወቀ

ድምጻችን ይሰማ የሚል መፈክር አንግበው ላለፉት አስራ ሶስት ወራት አፋኙን የወያኔ አገዛዝ መቆሚያና መቀመጫ በማሳጣታቸው በጭካኔ እስር ቤት የተጣሉት ሙስሊም ኢትዮጵያዊያን ከፍተኛ ችግር ላይ መውደቃቸውን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ባስተላለፈልን ሪፖርት ገለጸ። እንደዘጋቢያችን ሪፖርት በዘረኛውና አረመኔው የወያኔ አገዛዝ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች ታፍሰውና ማእከላዊ እስር ቤት ውስጥ በግፍ ታስረው የሚገኙት ሙስሊም የዩኒቨርስቲ ተማሪዎች፣ ቤተሰቦቻቸው ያሉበትን ቦታ ባለማወቃቸው በቀለብ እና በልብስ እጦት እየተቸገሩ ነው ብሏል።

ዘጋቢያችን እንደገለጠው በአቃቂ እስር ቤት በመቶዎች የሚቆጠሩ ሙስሊም ተማሪዎችና መምህራን እስር ቤቱን አጨናንቀው እንደሚገኙ ለማወቅ የተቻለ ሲሆን፣ ከነኝህ ታሳሪዎች ውስጥ እጂግ በርካቶቹ ቶርቸር ( አሰቃቂ ድብደባ) ተፈጽሞባቸዋል። ይህም አልበቃ ብሎ ተማሪዎቹ በአሁኑ ጊዜ የረባ ምግብ አጥተው በመሰቃየት ላይ እንደሚገኙና ልብሶቻቸው በላያቸው ላይ እያለቁባቸው ለእርዛት እየተዳረጉ እንደሆነም ታውቋል።

አሁንም ጭካኔአዊ አሰራው አለማብቃቱና የተለያዩ ታማሪዎች በየጊዜው እየተያዙ መሆኑን የገለጸው ዘጋቢያችን በማእከላዊ እስር ቤቶች ውስጥ ታስረው ከሚገኙት መካከል የባህርዳር ዩኒቨርስቲ ተማሪ የሆኑት ኑርየ ካሲም እና ካሊድ ሙሀመድ፣ የጅማ ዩኒቨርስቲዎቹ ያሲን ፈይሞ፣ ሙሀመድ አሚን ከድር፣ እና ጁነዲን ሁሴን፣ የሚዛን ተፈሪው አብዱላኪም አህመድ፣ የወሎ ዩኒቨርስቲዎቹ ጣሂር ሙሀመድ ፣ ሙሀመድ አብዱራሂም እና ሰኢድ ሙህዲን፣ የጎንደር ዩኒቨርስቲዎቹ ሰኢድ አብርሀም፣ አማር ሙሀመድ፣ እና ሊና፣ የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲው አብዱላዚዝ ሰኢድ እንዲሁም የአዋሳ ዩኒቨርስቲዎቹ አብደላ ሙሀመድ ይገኙበታል ብሏል።

የሙስሊም ጉዳይ አምደኛ የነበረው ሶሎሞን ከበደ፣ የከሚሴው ዳኢ ጀማል ከበደ፣ የሻሽመኔው ዳኢ አብዱረዛቅ ሼህ አህመድ፣ የከሚሴው ዳኢ ኢክርሀም አብዱ፣ የሀረርጌው ሁሴን ሮባ፣ የድሬዳዋው ሙሀመድ ሀሰን፣ የከምሴው ሁሴን አሊ እና አደም አህመድ አሊ በማእከላዊ እስር ቤት ከታሰሩትና ከፍተኛ ስቃይ ከደረሰባቸው መካከል ይገኙበታል።

የወያኔ ኢህአዴግ ፈረስ የሆነው ሀይለማርያም ደሳለኝ የሙስሊሙን እንቅስቃሴ ለመቆጣጠር እርምጃ እንወስዳለን በማለት ሰሞኑን በባህርዳር በመካሄድ ላይ ባለው የወያኔ ኢህአዴግ ጉባኤ ላይ መዛቱንም ተያይዞ የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

## የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

ለህዝብ ይፋ ያደረገዉ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል ከተለያዩ አቅጣጫዎች የሚመጡ አያሌ ኢትዮጵያዉያን በየቀኑ እየተቀላቀሉት ሲሆን ይህንን የህዝብ ተገንና አለኝታ የሆነ ኃይል በመቀላቀል የአዲስቷ ኢትዮጵያ ትንሳኤ ለመሆን የምትፈልጉ በአገር ዉስጥም ሆነ በዉጭ አገራት የምትገኙ ኢትዮጵያዉያን ህዝባዊ ኃይሉ በተከታታይ ለሚያወጣቸዉ መግለጫዎችና ህዝባዊ ጥሪዎች ምላሽ በመስጠት እንዲትተባበሩ የግንቦት ሰባት ህዝባዊ ኃይል ጥሪዉን ያስተላልፋል።

## ወያኔ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ያፈናቀላቸዉ 59 የአማራ . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

መኪኖች ወደ አማራ ክልል የተጓዙ ሲሆን፣ ሁለቱ ህጻናት በመንገድ ላይ የሞቱት አየር አጥሯቸው ሲሆን ህጻናቱን እናታቸው በወጉ አልቅሳ በወጉ ሳትቀብር በረሀ ላይ እንዲጣሉ መደረጋቸውን ነዋሪዎች ገልጸዋል ብሏል ኢሳት። ከዚሁ በተጨማሪም በሌላ መኪና የተሳፈረች አንድ ሌላ ህጻንም እንዲሁ አየር አጥሯት ስትደክም ፣ ሾፌሩ አቁሞ ህክምና እንድታገኝ ያደረገ ሲሆን አካባቢውን እንዲለቁ ከተጠየቁት አማሮች መካከል ደግሞ ሁለት ሰዎች ታርደው መገኘታቸውን ግለሰቡ ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ደረሰን ዜና እንደሚያስረዳዉ አሁንም በቤንሻንጉል ጉሙዝ አካባቢ በርካታ አርሶ አደሮች በክልሉ ልዩ ሚሊሺያ ጥቃት እንደደረሰባቸው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል። በአማራዉ ላይ እየደረሰ ያለዉን ጥቃትና መፈናቀል አስመለክቶ አንድ የክልሉ ከፍተኛ ባለስልጣን ከአዲስ አድማስ ጋዜጣ ጋር ባደረገዉ ቃለ ምልልስ ተፈናቃዮቹ የአማራ ተወላጆች በህገወጥ መንገድ ወደ ክልሉ የገቡ ናቸው የሚል ዘረኞች ያስተማሩትን መልስ ሰጥቷል። አዲስ አበባ ድረስ ስልክ ደዉለን ያናገርናቸዉ አንድ የህግ ባለሙያ አንደተናገሩት ጋምቤላ ዉስጥ የአኝዋኮችን መሬት ቀምቶ ለትግራይ ባለሀብቶችና ለዉጭ አገር ዜጎች የሰጠዉ ዘረኛዉ የወያኔ አገዛዝ ለምን አማራዉን እየመረጠ ከየክልሉ እንሚያባርር አይገባኝም ካሉ በኋላ ጋምቤላ የትግራይ ተወላጆች የትዉልድ ቦታ ላትሆን ትችላለች ሆኖም ገራፈርዳ፤ ጋምቤላም ሆነ ቤንሻንጉል ጉሙዝ አማራዉ፤ ትግሬዉና የአካባቢዉ ተወላጆች ከሌሎች ኢትዮጵያዉያን ጋር እኩል የሚጋሯቸዉ ቦታዎች ናቸዉ እንጂ፤ አማራን ከየገባበት እያባረሩ ለትግራይ ተወላጆች ግን ኗሪዉን እያፈናቀሉ መሬት መስጠት ፋሺስት ጣሊያን እንኳን ያላደረሰዉ በደል ነዉ ብለዋል።

የህግ ባለሙያዉ ንግግራቸዉን በመቀጠል የኢትዮጲያ ህገመንግስት አንቀፅ 32 “የመዘዋወር ነፃነት” በሚል ርእስ ስር ‹‹ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ አገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ፤ በመረጠው የአገሪቱ አካባቢ የመኖርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከአገር የመውጣት መብት እንዳለው ይደነግጋል፤ ሆኖም የኢትዮጲያ ህገመንግስት የወያኔ ማጥቂያ መሳሪያ በመሆኑ ወያኔ ከዚህ ቀደም በአርሲ፤ በሀረርና በቅርቡ ደግሞ በጉራፈርዳ እንዳደረገዉ አሁን ደግሞ በቤንሻንጉል ክልል የአማራን ተወላጆች ለማጥቃት ተጠቅሞበታል ሲሉ ወያኔን አጥብቀዉ ኮንነዋል።

### የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።

<u>መካከኛ ሞገድ</u>:- በ 358 MB, በ 837 kHz

<u>አጭር ሞገድ</u>:- በ 31 MB በ 9700 KHz

**በ 41 MB በ 7185, በ 7175 በ 7160 እና በ 7120 KHz**

**በ 49 MB በ 5980 KHz እና በ 60 MB 4760 GHz**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ እና ሐሙስ ከጠዋቱ 2፡30 እስከ 3፡00 ሰዓት በድጋሚም ከሰዓት በኋላ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት እንዲሁም ዘወትር ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 እስከ 3፡30 ሰዓት እንዲሁም ከሰዓት በኋላ ከምሽቱ 11፡30 እስከ 12፡00 ሰዓት የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፣ **በስልክ** ወይም **በኢሜል** በንቅናቀያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

<u>ማሳሰቢያ</u>:- ሰዓቱ በኢትዮጵያ የሰዓት አቆጣጠር ነው።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org